Davos

ዳቮስ- ***Davos, Switzerland***
ዳቮስ የተባለችው ከተማ የስዊትዘርላንድ ትንሽ ከተማ ነች። ይህች ከተማ አንድ መለያ አላት። ይህም የአለም ኢኮኖሚክ ፎረም ነው። ስለ ዳቮስ ከተማ ና ልዩ  ነገሮቿ በዚች ጽሁፍ አብራርቻለሁ።

ስዊትዘርላንድ ላንድሎክድ ወይም ባህር በር አልባ ና ተራራማ የ አውሮፓ ሃገር ናት።ስዊትዘርላንድ ፌደራላዊ ሀገር ስትሆን የ 26 ካንተን ስብስብ ናት። ሃገሪቱ በሰሜን ከጀርመን፣በደቡብ ከጣሊያን፣ በምእራብ ከፈረንሳይ እንዲሁም በስተምስራቅ ከኦስትሪያ ና ሌችንስታይን ጋር ትዋሰናለች።ሃገሪቱ 41.3 ሺ ስክዌር ኪሎሜትር የቀዶ ስፋት አላት።በነገራችን ላይ ስፋቷ በኢትዮጵያ ከምትገኘው ትግራይ ክልል ቆዳ ስፋት በ 9 ሺ ስክዌር ኪሎሜትር ያነሰ መሆኑን ልብ ይሏል።

ይህ ጽሁፍ በተጻፈበት ወቅት የ ስዊትዘርላንድ ህዝብ ብዛት 8.5 ሚሊዮን  ነበር።ሶስት ታላላቅ ከተሞች አሏት።የፖለቲካ ማእከሏ ጄነቭ (*Geneva*) ፣የዲያመንድ ሊግ አስተናጋጇ ዙሪክ (Zürich) ና ባዜል ዋና ዋናዎቹ ከተማዎች ናቸው።አለም ጤና ድርጅት፣ የአለም ንግድ ድርጅት፣ የአለም ላብ አደሮች ድርጅት ና ፊፋ ዋና መቀመጫዎች በእነዚህ ከተሞች ነው።ታዋቂው የቀይ መስቀል ድርጅት ውልደቱን በዚህች ሃገር አድርጓል።

ዳቮስ ከተማ ግራውቡንደን በተባለች የስዊትዘርላንድ ግዛት የምትገኝ ከተማ ነች።ይህች ከተማ ላንድዋሰር የተባለ ወንዝ ጥግ የምትገኝ አስገራሚ ከተማ ነች። ይህች ከተማ 10 832 ቋሚ ኗሪዎች አሏት። ከተማዋ በጣም የምትታወቀው የአለም ኢኮኖሚክ ፎረምን በየአመቱ በማስተናገዷ ነው።ዳቮስ በመዛግብቶች ላይ የተጠቀሰችው በ 1213 ሲሆን ስሟም ታቩስ ነበር። በ 19 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን  ግማሽ ላይ የዳቮስ ከተማ ህክምና በሚሹ ሰዎች የምትጎበኝ ከተማ ሆነች። ይህም የሆነበት ምክንያት አንድም የዳቮስ አየር ንብረት በጣም ምቹ ስለነበር ና ታዋቂ የሳምባ ሃኪሞችን አቅፋ ስለነበር ነው። እውቁ የግዜው የቲቢ በሽታ ሃኪም ዶ/ር አሌክሳንደር ስፔንግለር (Alexander Spengler). በ 1880 እውቁ ደራሲ ና ገጣሚ ሮበርት ሉዊስ ስቴቬንሰን(Rober Louis Stevensen) በቲቢ በሽታ የታመመ ግዜ በዳቮስ ከተማ ቆይቶ  ህክምና ተደርጎለታል።

ይች ከተማ ከባህር ወለል 1560 ሜትር ከፍታ በላይ ትገኛለች። የቆዳ ስፋቷ 284 ስክዌር ኪሎ ሜትር ነው።የዳቮስ ሲሶው (35%) ያህሉ ለግብርና አገልግሎት ይውላል።ወደ ሩብ የሚጠጋው （22.2%）የዳቮስ ቦታ በጫካ የተሸፈነ ሲሆን 2.3 በመቶው ለግንባታና ለመንገድ አገልግሎት ዉሏል። ቀሪው 40% ቦታ ደግሞ ለልማት የማይውል ቦታ ነው።

ዳቮስ ለ 125 ቀናት ገደማ ዝናብ ታገኛለች።ከፍተኛ ዝናብ የምታገኘው ከሰኔ እስከ ነሃሴ ወር ነው። በአንጻሩ በጣም ደረቃማው ወር የካቲት ወር ነው።

ከላይ እንደተጠቀሰው ቋሚ የህዝብ ብዛት አላት። የህዝብ ብዛቷም 10 832 ነው። አብዛኛው ህዝብ (86.3% ) ጀርመንኛ ተናጋሪ ናቸው ።ክሮሽያ ና ጣሊያንኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ተነጋሪ ቋንቋዎች ናቸው።በ 2014 ዳቮስ 5441 ቤቶች ሲኖሯት እያንዳንዱ ቤት በአማካይ 2 ሰዎችን ይዟል።

ሰባ አራት በመቶ የዳቮስ ህዝብ ቢያንስ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተምረዋል።ኢኮኖሚዋ በቱሪዝም በእጅጉ ይታገዛል። የህዝቡ ሃይማታዊ ስብጥር እጅግ ያስገርማል። ሁሉም አብራሃናዊ ሃይማኖቶች በዚች ቦታ ተከታይ ያላቸው ሲሆን የካቶሊክ ክርስትና በብዙሃኑ ይመለካል። እኔን የገረመኝ የኦርቶዶክስ ና እስልምና ተከታይ መኖሩ ነው።439 (3.9%)የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ተከታዮች ና 79 (0.7%) የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በዚች ከተማ ህይወታቸውን ይመራሉ።